DHHS
MONTGOMERY COUNTY
Department of Health and Human Services

# የግል ምስጢር ጥበቃ አሰራሮች ማስታወቂያ

**ይህ ማስታወቂያ የእርስዎ የጤና እና የግል መረጃዎ እንዴት በጥቅም ላይ እንደሚውል ወይም እንዴት ለሌላ እንደሚገለጽ እንዲሁም እርስዎ ይህንን መረጃ እንዴት ለማየት እንደሚችሉ ይዘረዘራል። እባክዎ ይህንን በጥንቃቄ ይመልከቱ።**

## አገልግሎቶቻችን እና የምንሰበስበው መረጃ

የሞንትጎሜሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች ክፍል (ዲኤችኤችኤስ) አንድ ትልቅ የልዩ ልዩ አገልግሎቶች ድርጅት ሲሆን የሚሰጣቸው አገልግሎቶችም የጤና፣ የአእምሮ ጤና፣ የተከለከሉ ዕጽዋት መጠቀም፣ የልጅ ደህንነት የገቢ ድጋፍ እና ሌሎች ህብረተሰብ አገልግሎቶች ናቸው። አገልግሎቶችን ለእርስዎ ለመስጠት የዲኤችኤችኤስ ሰራተኞች ብዙ የግል መረጃዎችን ይጠይቁዎታል፤ በመዝገብዎ ውስጥም ያስቀምጥዋቸዋል። ይህ መረጃ የሚከተሉትን ይጨምር ይሆናል።

- እንደ ስምዎ፣ አድራሻዎ፣ የስልክ ቁጥሮ፣ የልደት ቀን እና ሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር ያሉ ማንነቶን የሚያረጋግጡ መረጃዎች
- የገንዘብ መረጃ፤ ይህ መረጃ የሚካታትተው ስለ ገቢዎ፣ በባንክ ያሉትን ሂሳቦች ወይም ሌላ ሃብት እንዲሁም ያለዎትን ማናቸውንም የኢንሹራንስ ሽፋን
- በምስጢር የሚያዝ የጤና መረጃ ስለ አለፈው፣ ስለ አሁኑ ወይም ስለወደፊቱ የጤና ወይም አእምሮ ጤና ህክምና የሚነግረንን ማናቸውንም መረጃ ይጨምራል።
- ስለ ጥቅሞች መረጃ ወይም እርስዎ አሁን ስለሚያገኙዋቸው ወይም ስለተሰጡዎ አገልግሎቶች።

## የኛ ሃላፊነቶች

የርስዎን የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎችን ምስጢርነት የፌዴራል እና የስቴት ህጎች ይጠብቃሉ። እኛም እነዚያን ሁሉ ህጎች አክብረን እንከተላለን። መረጃዎን በደህና ሁኔታ ጠብቀን ለማስቀመጥ ተገቢ እርምጃዎችን እንወስዳለን፤ መረጃዎን እንጠቀምበታለን። (በዲኤችኤችኤስ ውስጥ እንጋራለን)። እንዲሁም ለሌላ እንገልጻለን። (ከዲኤችኤችኤስ ውጭ እናጋራለን)። ይህንንም የምናደርገው ስራችንን ለማከናወን አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ እና በህግ በተፈቀደ ወይም በታዘዘ ጊዜ ብቻ ይሆናል። ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በስተቀር በሌላ ምክኒያት የርስዎን መረጃ  እና መጠቀም ወይም ለሌላ መግለጽ ካስፈለገን፣ የእርስዎን የጽሁፍ ፈቃድ እንጠይቃለን። የሰጡንን ማናቸውም የጽሁፍ ፈቃድ የመሰረዝ መብት አለዎ። የሰጡትን ፈቃድ ከሰረዙ፣ የሰጡንን ፈቃድ መሰረት በማድረግ ቀደም ሲል ያደረግነውን የመረጃዎ መጠቀም ወይም መግለጽ አይመለከትም።

ይህንን የግል ምስጢር ጥበቃ አሰራሮች ማስታወቂያ እንድንሰጥዎ እና ተከታትለን እንድንፈጽም ህግ ያስገድደናል። የዚህን ማስታወቂያ አንቀጾች እና የግል ምስጢር ጥበቃ አሰራሮችንን ለመለወጥ እና ይህም ለውጥ እኛ ዘንድ ባስቀመጥናቸው የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ለማድረግ መብት አለን። በሚቀጥለው ቢሮአችንን በሚጎበኙበት ጊዜ በግል ምስጢር ጥበቃ አሰራራችን ላይ ስለተደረጉ ማናቸውም ለውጦች በእንግዳ መቀበያ ክፍሎቻችን እና በዲኤችኤችኤስ ድረ ገጽ ላይ በ www.montgomerycountymd.gov  ይገኛል።

## እንዴት ያለ እርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ መረጃ እንደምንጠቀም ወይም ለሌላ እንደምንገልጽ

- **ለህክምና እና አገልግሎቶች፤**

ከርስዎ ጋር የሚሰሩ የዲኤችኤችኤስ ሰራተኞች ለእርስዎ የተቀነባበረ ህክምና እና አገልግሎቶች ለመስጠት የእርስዎን የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎች ይጠቀሙባቸው ይሆናል። ዲኤችኤችኤስ የጤና ነክ እና ሌሎች የግል መረጃዎችዎን ለማስቀመጥ የተዋቀረ የኬዝ አስተዳደር ስርዓት ዘርግቷል። ከአሁን በፊት ከሄዱባቸው የጤና አገልግሎት ሰጪዎች፣ እርስዎ ላይ ምርመራ ካደረጉ ሌሎች የጤና ጥበቃ

ተቋሞች፣ የጤና ኢንሹራንስ እቅድዎ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ እርስዎን ከሚንከባከብዎ የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ መረጃዎችን ልንሰበስብ እንችላለን። ከእርስዎ የህክምና መረጃ ውስጥ የተወሰነው ወይም ሙሉውን በኤሌክትሮኒክ ፎርማት ሊፈጠርለት ወይም/እና ሊቀመጥ ይችላል። ምሳሌዎች፣

- ከክሊኒኮቻችን ውስጥ ባንዱ የጤና እንክብካቤ የሚያገኙ እና ለሌላ እንደ መኖሪያ ቤት እርዳታ ወይም የገቢ ድጋፍ ለማግኘት: ለማመልከት ከፈለጉ፣ የርስዎን ጉዳይ የያዙት ሰራተኛ ወደ ሌላ በመምራት እና የብቁነት መረጃን በመጋራት እነዚህን አገልግሎቶች እንዲያገኙ ይረዱዎት ይሆናል።
- ከአንድ በላይ የዲኤችኤችኤስ አገልግሎት የሚቀበሉ ከሆኑ፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ አንድ የተቀነባበረ ዕቅድ ለማውጣት የእርስዎን ጉዳይ የያዙት ሰራተኞች እርስ በርሳቸው ለመነጋገር ይቻላሉ

ለተገቢው አላማ ሲፈለግ (ለምሰሌ፣ ህክምና ሊሰጥዎ ወይም ለአገልግሎት ክፍያ ሲጠየቁ) የጤና አገልግሎት አቅራቢዎች የጤና መጃዎን ሊያገኙ ይችላሉ። ሌሎች ለእርስዎ ህክምና የሚሰጡ ከ ዲኤችኤችኤስ ውጪ ያሉ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች የኤሌክትሮኒክ መረጃዎን ሊያገኙ ይችላሉ።

የዲኤችኤችኤስ ሰራተኞች የርስዎን መረጃ ለህክምና እና ለአገልግሎት ከዲኤችኤችኤስ ድርጅቶቻችን *ውጭ* ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚጋሩት በርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ወይም በፌዴራል ወይም በስቴት ህግ በተፈቀደው መሰረት ይሆናል። ለምሳሌ፣ የጤና እንክብካቤ የሚያደርጉልዎ የኛ የዲኤችኤችኤስ ሰራተኞች የርስዎን የጤና መረጃ ህክምና እያደረጉልዎ ላሉ የውጭ ተንከባካቢዎች እንዲያጋሩ የፌዴራል እና የስቴት ህግ ይፈቅዳል።

**<u>ከኛ የአእምሮ ጤና አገልግሎት የሚጠቀሙ ከሆነ፥</u>**

- የአእምሮ ጤና መረጃዎ ለእርስዎ ህክምና ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ሲባል ያለፈቃድዎ እናጋራ ይሆናል፤ የምናጋራው ግን ህክምናዎን ወይም አገልግሎቶን የሚመለከት ብቻ ይሆናል።
- የህክምና አገልግሎት አቅራቢዎቻችን የተሻለ የህክምና ውሳኔ እንዲያደርጉ እና የጤና እንክብካቤዎን ለማመቻቸት የርስዎን የጤና እና አእምሮ ጤና መረጃ የተመለከት አንድ ኤሌክትሮኒክ መዝገብ እናስቀምጣለን።
- በአብዛኛው የሳይኮቴራፒ ጽሁፎችዎን የምናጋራው በርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ብቻ ነው። ሳይኮቴራፒ ጽሁፎች በህግ እንደተደነገገው በአእምሮ ጤና ሀኪም ተዘጋጅተው ከጤና ማህደርዎ ተለይተው የሚቀመጡ ናቸው። በአጠቃላይ፣ ሰራተኞቻችን ሁሉንም ጽሁፎችዎን በጤና ማህደርዎ ላይ፣ የሳይኮቴራፒ ጽሁፎችዎን ሳይለዩ፣ ጠቅልለው በጋራ ያስቀምጣሉ።
- የአልኮል ወይም የተከለከሉ ዕጽዋት መጠቀም ማህደሮችዎን የሚከተሉትን ካላደረጉ በስተቀር አናጋራም፤
  - የጽሁፍ መረጃ ሲሰጡን፤
  - መረጃው በፍርድ ቤት ትእዛዝ መገለጥ ሲችል፤
  - መረጃው ለህክምና ባለሙያዎች በድንገተኛ ህክምና ወይም ለተመረጡ ባለሙያዎች ለጥናት፣ ቁጥጥር ወይም የፕሮግራም ግምገማ ሲገለጥ፤
  - መረጃውን ከእኛ ጋር መረጃን በጥንቃቄ ስለመጠበቅ ስምምነት ስላደረገ ለእርስዎ ህክምና ወይም የህክምና አገልግሎት አቅራቢ ስንጋራ፤ *እነዚህ ስምምነቶች የተከለከሉ ዕጽዋት መጠቀም ማህደሮችዎን ከዲኤችኤችኤስ የጤና እና አእምሮ ጤና አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር ለመጋራት የተቀመጡ ናቸው።*
- በህግ ከተደነገገው ሁኔታ በስተቀር የተበደሉ ሰዎች፣ የሰለባዎች እርዳታ እና የወሲብ ጥቃት ፕሮግራሞች መረጃዎችን ካለርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ አንጋራም። እነኚህ ፕሮግራሞች በእኛ የኤሌክትሮኒክ ሲስተም ውስጥ የተወሰኑ ናቸው።

አንዳንድ ፕሮግራሞቻችን "የትምህርት ማህደሮችን" በ 1974 የቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና ምስጢርነት ህግ (ኤፍኢአርፒኤ) መሰረት ያስቀምጣሉ። እነዚህን የርስዎ ማህደሮች ከርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ውጭ ለድንገተኛ ካልሆነ በቀር ለሌላ አገልግሎት አቅራቢዎች አናጋራም።

ዲኤችኤችኤስ በቼሳፒክ ያካባቢ መረጃ ሲስተም ለታካሚዎች (ክሪስፐ)፣ ያካባቢ መረጃ ልውውጥ (ኤችአይኢ) ይሳተፋል። በህግ እንደተፈቀደው፣ የጤና መረጃዎ ከዚህ ልውውጥ ጋር የሚጋራው የተሻለ እና የተዋቀረ እንክብካቤ ለመስጠት አገልግሎቶች አቅራቢዎችና የህዝብ ጤና ሰራተኞች እንዲመቻቸው ነው። ከዚህ መጋራት ለመውጣት ከፈለጉ እና የጤና መረጃዎ በክሪስፐ ተፈልጎ እንዳይገኝ ከፈለጉ፣ በ 1-877-952-7477 በመደወል እና የአፕት አውት ቅጽ በፖስታ፣ በፋክስ ወይም በ www.crisphealth.org በመሙላት ይችላሉ። በክሪስፐ ከመካተት ለመውጣት ከፈለጉ፣ የጤና አግልግሎት አቅራቢዎችዎ ኤችአይኢን የላብራቶሪ ውጤትዎን፣ የራጅ ውጤትዎን፣ እና ሌላ የሚላክላቸውን መረጃ በፋክስ ወይም በፖስታ ወይም በሌላ ኤሌክትሮኒክ መንገድ ያገኙትን ጨምሮ መረከብ ይችላሉ። በህግ የተፈቀደ የህዝብ ጤና ማጠናቀር፣ እንደ የተላላፊ በሽታ ጥንቅር ለህዝብ ጤና ሰራተኞች የሚውል መረጃ፣ በ ኤችአይኢ በኩል እርስዎ ከወጡ በሁዋላም ይተላለፋል።

**DHHS ዳይሬክቶሪ፡** ካልተቃወሙ በስተቀር እንደ ስምዎ እና አጠቃላይ ዲሞግራፊያዊ መረጃዎን የመሳሰሉ የጤና ነክ መረጃዎን ለዳይሬክቶሪያችን ልንጠቀም እንችላለን። በዳይሬክቶሪያችን ውስጥ የተካተተው መረጃ ከጤና እና ከሰብአዊ አገልግሎቶች ጋር ተዛማጅ ከሆኑ ግለሰቦች ጋር ያለ እኛ ፈቃድ ይፋ አይደረግም።

- **ለክፍያ፤** ለተደረገልዎ የጤና ወይም የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ክፍያ ለመቀበል እንዳላስፈላጊነቱ የእርስዎን የጤና ወይም የግል መረጃ እንጠቀምበት ወይም እንጋራ ይሆናል። ለምሳሌ፥ ለተደረገልዎ ህክምና ከሜዲኬድ ወይም ከሜዲኬር ክፍያ ለመጠየቅ መረጃዎን እንጠቀም ይሆናል።

- **ለጤና እንክብካቤ፣ የስራ እንቅስቃሴዎች፤** የእኛን ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ለማስተዳደር የእርስዎን የጤና ወይም የግል መረጃ እንጠቀምበት ወይም ለሌላ እንገልጽ ይሆናል። ለምሳሌ፣ በክፍሉ በኩል የሚያገኙትን የአገልግሎት ጥራት ለመመርመር ጉዳይዎን መዝገብ የዲኤችኤችኤስ ሰራተኞች ወይም የውጭ ኦዲተሮች ይመለከቱ ይሆናል።

- **ለቀጠሮዎች ወይም ለማስታወቂያዎች፤** ቀጠሮ ለመያዝ ወይም ስለ ቀጠሮ ለማስታወስ፣ ወረቀት ጽሁፎችን ለማጠናቀቅ፣ ሊፈልጉዋቸው ስለሚችሉ ስለሌሎች የተዛመዱ አገልግሎቶች ጥቅሞች ወይም አገልግሎቶች ለማስታወቅ ወይም በድንገተኛ አደጋ ጊዜ ለመገናኘት ከእርስዎ ወይም ከተወካይዎ ጋር እንገናኝ ይሆናል።

- **የስራ ተባባሪዎቻችን፤** እንደ የገንዘብ ሂሳብ ወይም የህግ አገልግሎቶች፣ ዘገባ ትንተና፣ እና ችሎታ መረጋገጥን እንዲሁም የአገልግሎት ጥራት ማረጋገጫ ምርመራን ያሉ የአስተዳደር እና የድጋፍ አገልግሎቶች ከሚያቀርቡ ከዲኤችኤችኤስ ውጭ ከሆኑ ሰዎች ጋር ስምምነቶች አሉን። እነዚህ ሰዎች የስራ ተባባሪዎች ተብለው ይጠራሉ። እነዚህን አገልግሎቶች ለርስዎ እንዲሰጡዎ የእርስዎን መረጃ ለስራ ተባባሪዎች እንገልጽ ይሆናል። ሆኖም የስራ ተባባሪዎች እንገልጽ ይሆናል። ሆኖም የስራ ተባባሪዎች የርስዎን መረጃ በጥብቅ ምስጢርነት እንዲይዙ እናዝዛቸዋለን።

- **የእርስዎ ቤተሰብ፤ ጓደኞች እና በእርስዎ እንክብካቤ የሚሳተፉ ሌሎች** የርስዎን መረጃ ለርስዎ ቤተሰብ፣ እና በርስዎ እንክብካቤ የሚሳተፉ ሌሎች እንገልጽ ይሆናል። ለምሳሌ፣ የቤት ውስጥ እንክብካቤን ከምታዘጋጅ ወይም ከሚያዘጋጅ አካለ መጠን ለደረሰ ወይም ለደረሰች ልጅዎ ጋር ስለ የህመምዎ ሁኔታ እንወያይ ይሆናል። ይህንን መረጃ ከቤተሰብዎ ጋር እንዳንጋራ ከፈለጉ፣ ይህን ሊጠይቁ ይችላሉ እኛም አናደርግም። እርስዎ በጽሁፍ ፈቃድ ካልሰጡን በስተቀር ስለ አእምሮ ጤናዎ ወይም ስለ ተከለከለ ዕጽዋት አላግባብ መጠቀም ታሪክዎ፣ ወይም በቤተሰብዎ ስለሚደረግልዎ እንክብካቤ የእርስዎን መረጃ አንጋራም።

- **ለመንግስት ፕሮግራሞች፤** እንደ ሶሻል ሴኪዩሪቲ ጥቅሞች ካሉ ሌሎች የመንግስት ፕሮግራም ጥቅሞች ብቁ እንደሆኑ ለማጣራት፣ የርስዎን የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎች እንገልጽ ይሆናል።

- **ለህዝብ ጤና ጥበቃ ተግባሮች፤** ለህዝብ ጤና ጥበቃ ተግባሮች የርስዎን የጤና መረጃ እንጠቀምበት ወይም ለሌላ እንገልጽ ይሆናል። ለምሳሌ፣ ለተላላፊ በሽታ ተጋልጠው ከሆኑ (በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፍ በሽታ) ይህንኑ ለስቴቱ እንገልጽ ይሆናል። እንዲሁም የዚህን በሽታ ስርጭት ለመከላከል ሌሎች እርምጃዎችንም እንወስድ ይሆናል።

- **ለጤና ቁጥጥር ተግባሮች፤** ህጉ በሚጠይቀው መሰረት ፕሮግራማችንን ለኦዲት፣ ምርመራ እና ፍቃድ ለመሳሰሉ የቁጥጥር ተግባር የሚያደርጉ ሌሎች መስሪያቤቶች የርስዎን መረጃ ልናጋራ እንችላለን።

- **ስለበደል እና ችላ ስለማለት ማስታወቅ እና ምርመራዎች፤** በልጆች ላይ እና በተጋለጡ አዋቂዎችም ጨምሮ፣በአዋቂ ላይም እንደ ልጅ ተፈጽሟል ተብሎ ስለሚጠረጠር በደል እና ችላ ማለት መግለጽና ማስታወቅ እንዳለብን ህግ ያስገድደናል። የጤና እና አእምሮ ጤና አገልግሎት አቅራቢዎች መረጃው ለምርመራ፣ ተጋላጭነት ጥናት፣ ወይም የአገልግሎት ወይም የጥንቃቄ ፕላን ይጠቅማል ብለው ካመኑ ለአዋቂ እና ህጻናት ጥበቃ አገልግሎት መረጃውን ሊያጋሩ ይችላሉ።

- **ጉዳትን ለማስወገድ፤** ዲኤችኤችኤስ በአንዳንድ ሁኔታዎች ስለ እርስዎ የጤና ወይም ሌላ የግል መረጃ ለህግ አስከባሪ ይገልጽ ይሆናል። ለምሳሌ፥ ከሰራተኞቻችን መካከል ባንዱ ላይ ወይም በሌላ ደምበኛ ላይ ጉዳት ካደረሱ ወይም በንብረታችን ላይ ጉዳት ካደረሱ ወይም ባለሙያ ሰራተኞቻችን እርስዎ በሌሎች ሰዎች ወይም በራስዎ ላይ ከባድ ጉዳት ያደርሳሉ ብለው ካመኑ፣ ለህግ አስከባሪ እናስታውቃለን። እንዲሁም ዲኤችኤችኤስ እንደ የአሸባሪ ጥቃት ወይም ድንገተኛ ደራሽ ከፍተኛ አደጋ ባጋጠመ ጊዜ የርስዎን የጤና ወይም ሌላ የግል መረጃ ይገልጽ ይሆናል።

- **ለሬሳ መርማሪዎች፣ የመቃብር ቤት ዲሬክተሮች የሞትን ምክንያት መርማሪዎች እና የአካል መስጠት።** ዲኤችኤችኤስ ሞትን የሚመለከት የጤና መረጃ ለሬሳ መርማሪዎች፣ የመቃብር ቤት ዲሬክተሮች እና እንዲሁም የአካል ክፍል፣ ዓይን፣ ስጋ መስጠት ወይም ለመተካት ለተፈቀደላቸው ድርጅቶች ይገልጽ ይሆናል።

- **ለምርምር ተግባር፥** ባንዳንድ ሁኔታዎች ለህክምና ምርምር ጥናት የርስዎን የጤና መረጃ እንጠቀምበት ወይም እንገልጽ ይሆናል። ላንዳንድ ጉዳዮች የርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ይፈለጋል። የምርምር ጥናቶች እና መግለጫዎች ሰዎችን በስም ለይተው አይገልጹም።

- **ለፍርድ ቤት ክርክሮች፥** በህግ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለፍርድ ቤቱ ስለርስዎ መረጃ እንድናቀርብ እንታዘዝ ይሆናል። የጤና መረጃዎን ለ ሰራተኞች ካሳ መጠይቅ ጉዳይ ሲባል እናጋራ ይሆናል።

- **ህግ በሚያዝዘው መሰረት፥** የርስዎን የጤና ወይም ሌላ የግል መረጃ እንድንገልጽ አንድ ህግ ወይም ደንብ የሚያዝዘን ከሆነ ይህንኑ መፈጸም አለብን።

- **ገንዘብ ለማዋጣት፥** በአጠቃላይ ከደንበኞቻችን ጋር ገንዘብ የማዋጣት ስራ ላይ አንሳተፍም፣ ሆኖም ለገንዘብ ማዋጣት  ጥረቶች ካነጋገርንዎ፣ በድጋሚ እንዳናናግሮ ሊያሳውቁን ይችላሉ።

- **ከህልፈተ ህይወት በኋላ የጤና መረጃ መገኘት።** DHHS የጤና ነክ መረጃዎች ህይወትዎ ካለፈ በኋላ እስከ ሃምሳ (50) አመት ድረስ ያለፈቃድዎ መጠቀም ወይም ይፋ ማድረግ ይችላል። ይህንን ይፋ ማድረረግ የመገደብ መብት አለዎት።

## የርስዎን መረጃ የሚመለከቱ መብቶችዎ

**የሚከተሉት መብቶች አሉዎት፤**

- የግል ምስጢር ጥበቃ አሰራሮች ማስታወቂያ አንድ ቅጂ የማግኘት። ጥያቄ ሲቀርብ ይህ ማስታወቂያ በተለያየ ቅርጽ ይቀርባል።
- ሁልጊዜ ከምንገናኝበት ይልቅ ሌላ ስፍራ እንድንገናኝዎ ወይም ሌላ ዘዴ በመጠቀም እርስዎ ጋር እንድንገናኝ እኛን ለመጠየቅ። ለምሳሌ፣ ከቤትዎ መጥተን ከመገናኘት ይልቅ በስልክ ወይም በደብዳቤ እንድንገናኝዎ ሊጠይቁ ይችላሉ።
- ስለርስዎ ያስቀመጥነውን መረጃ ማየት፣ መመርመርና ቅጂ ማግኘት። *ይህንን ጥያቄ በጽሁፍ ማቅረብ አለብዎ፥* የመረጃዎን ቅጂ ለማዘጋጀት ለሚያስፈልገው ወጭ ክፍያ እንዲያደርጉ ይጠይቁ ይሆናል። መረጃዎን ለመመርመር ወይም ቅጂ ለማግኘት መብትዎን የማንሰጥባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። ይህ ከሆነ፥ ለምን ይህንን ውሳኔ እንዳደረግን እንዲሁም እምቢታው እንደገና እንዲመረመርልዎ እንዴት እንደሚጠይቁ ወይም እንዴት የአቤቱታ ፋይል እንደሚከፍቱ።
- እኛ ያስቀመጥነው መረጃ የተሳሳተ ወይም ያልተሟላ ነው የሚል ስሜት ካለዎ፥ መረጃዎ እንዲሻሻል (እንዲለወጥ) ጥያቄ ማቅረብ። *ይህንን ጥያቄ በጽሁፍ ማቅረብ አለብዎ።* በአንዳንድ ሁኔታዎች ለውጡን እንድናደርግ አንገደድም። ለውጡን ለማድረግ ካልተስማማን ለምን እንደሆነ እንገልጻለን። እንዲሁም ከኛ እንቢታ ጋር ባለመስማማት የጽሁፍ መግለጫ ለኛ ለመስጠት ስላለዎ መብት እንገልጽልዎታለን።
- ከጠየቁበት ከስድስት ወር በፊት ወዲህ የስርዎን መረጃ ስላደረግነው ዝርዝር መግለጫ ማግኘት (አንድ ግልጽ ዝርዝር)። ይህ መግለጫ ለህክምና፣ ለክፍያ ወይም ለጤና እንክብካቤ ዓላማ ለሌላ መግለጽ ወይም በርስዎ ፈቅደውልን ያደረግነውን ለሌላ መግለጽ አይጨምርም። *ይህንን ጥያቄ በጽሁፍ ማቅረብ አለብዎ።*
- የርስዎን መረጃ ለርስዎ ቤተሰብ እና ለሌሎች በርስዎ እንክብካቤ ለሚሳተፉ ሰዎች እንዳንጋራ ጥያቄ ማቅረብ።
- የጤና መረጃዎን ለህክምና እና አገልግሎት፥ ለክፍያ ወይም ጤና እንክብካቤ ተግባር ዓላማ እንዳንጠቀምበት ወይም ለሌላ እንዳንገልጽ ጥያቄ ማቅረብ። *እነዚህ ጥያቄዎች በጽሁፍ መቅረብ አለባቸው።* ለነዚህ ጥያቄዎች ተስማምተን እንድንፈጽም አንገደድም። ከተስማማን ግን፤ ለርስዎ ድንገተኛ አደጋ ህክምና መረጃውን መግለጽ ካላስፈለገን በስተቀር ስምምነቱን አክብረን መፈጸም አለብን። ጥያቄዎን ለመቀበልና ለመፈጸም ካልቻልን ለምን እንደሆነ እንገልጻለን።
- ለአገልግሎት ወይም ለጤና እንክብካቤ ከኪስዎ አውጥተው ሙሉ ለሙሉ ከከፈሉ፣ ለክፍያ ወይም ከጤና ኢንሹራንስ አቅራቢዎ ጋር ላለን ስራ መረጃውን እንዳናውለው መጠየቅ ይችላሉ። ህግ መረጃውን እንድናጋራ እስካልጠየቀን ድረስ የርሶን ጥያቄ ለማሟላት እንስማማለን።
- የርሶን መረጃ ለመሸጥ ወይም መረጃዎን ለግብይት ምክንያት ለማጋራት ከፈለግን የርሶን የጽሁፍ ፍቃድ እንድናገኝ መጠየቅ ይኖርብናል።
- መብትዎን የጣስን መስሎ ከተሰማዎት የክስ አቤቱታ ማቅረብ ወይም ችግርዎን መግለጽ ይችላሉ። የክስ አቤቱታ በማቅረብዎ አንዳችም ተቃራኒ እርምጃ አንወስድብዎትም። የክስ አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ችግርዎን ለመግለጽ የሚስጥርነት ባለስልጣኑን በሚከተለው አድራሻ ያነጋግሩ።

Privacy Officer
Montgomery County Department of Health and Human Services
401 Hungerford Drive
Rockville, MD 20850
240-777-1295 (Voice)
PrivacyMatters@montgomerycountymd.gov

የክስ አቤቱታዎ ወይም ቅሬታዎ የርስዎን የጤና መረጃ የሚመለከት ከሆነ፣ ከሚከተሉት ጋር በመደወል መነጋገር ይችላሉ። U.S. Department of Health and Human Services. Phone No. 1-877-696-6775.

## ጥያቄ እንዴት እንደሚቀርብ

ስለኛ የግል ምስጢር ጥበቃ አሰራሮች ጥያቄ ካለዎ ወይም ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ማንኛውንም ከፈለጉ፣ ከርስዎ ጋር ከሚሰሩት ሰራተኛ ጋር ይገናኙ፤ ወይም በዚህ ማስታወቂያ መጨረሻ ላይ አድራሻቸው ከተዘረዘረው የኛ የምስጢርነት ባለስልጣን ጋር ይገናኙ። በጽሁፍ መቅረብ ስላለባቸው ጥያቄዎች የዲኤችኤችኤስ የደንበኞች ጥያቄ ማቅረቢያ ቅጽ እንዲጠቀሙ እንጠይቃለን። ጥያቄ ማቅረቢያውን ቅጽ ከማናቸውም የዲኤችኤችኤስ ቢሮ ወይም የእኛ የምስጢርነት ባለስልጣን በመጠየቅ ማግኘት ይችላሉ።

በስራ ላይ የሚውልበት ቀን፥ ይህ ማሳሰቢያ ከጃንዋሪ 23, 2017 ጀምሮ በስራ ላይ ውሏል። 7/19